# አገርና አንድነትን የሚያፈርስ የአንድነት ልፈፋ!

የተለመደው የሴራ ፖሎቲካ የግንቦት ሰባት አባላት ነን በሚሉ ማፍያዎች መቀጠሉ የሀገራችንን ተስፋ ለሚጠባበቁ ሃይሎች አሳዛኝ ነው። በአንድነት ስም አፍራሽ ፕሮፕጋንዳ መንዛቱ ለምን እንደሚያስፈልግ የሚያውቁት ደራሲዎቹ ብቻ ናቸው። ጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ጸጋየ ሰሞኑን አዲስ አበባን በተመለከተ በሰጠው አስተያየት እየዎረደበት ያለው ውርጅብኝ ከአክራሪ ጎሰኛ ድርጅቶች ብቻ ቢሆን ተገቢ ነው ሊባል በቻለ ነበር። በኦነግና መሰሎቹ የሚነሳው አዲስ አበባ የኦሮሞ ነች የሚል ጉንጭ አልፋ ክርክር የሚጠበቅ ነው። በተደራጀ መረጃና ማስረጃ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ እንጂ የአንድ ጎሳ ንብረት አለመሆኗን መሞገትም እንችላለን። ነገር ግን የዜግነት ፖለቲካን አራምዳለሁ ከሚልና ድብቅ ተልዕኮ ካለው በተለይም ግንቦት ሰባትን ከሚመስሉ ድርጅቶች አባላት የሚሰነዘረው የማፍያ አይነት ጉዞ የትም አያደርስም።

በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ላይ ፣ በጋዜጠኛ ቴዮድሮስ ጸጋየ ላይ፣ በጋዜጠኛ ታምራት ነገራ ላይ፣ በጋዜጠኛና አክቲቪስት ሪዮት አለሙ ላይ፣ በአክቲቪስት አቻምየለህ ታምሩ ላይ እንዲሁም በአብንና በሌሎችም ጠንካራ አመለካከት ባላቸው ሰዎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ አንድ አይነት የፍረጃ ፕሮፓጋንዳ ሲነዛባቸው መስማት በጣም ያሳዝናል። ከነዚህ ሁሉ ጀርባ ያለው ኦነግ ነው ወይም ወያኔ ነው ማለት ግን ራስን ማሞኘት ነው። በማፈራረስና አጋጣሚዎችን ሁሉ ለራስ ጥቅም በመቀየር የሚታዎቁት ዶክተር ብርሃኑ ማፍያዎችን መሰብሰብ ስራቸው እስኪመስል ድረስ ጋዘጠኞቻችንንና የመብት ተሚጋቾቻችንን አንገት ለማስደፋት የሚሄዱበት አካሄድ ሁሉ የተበላ እቁብ መሆኑ ሊረዱት ይገባል። ቴዎድሮስን የወያኔ አሽከር፣ የለውጡ ተቃዋሚ ወዘተ በማለት ወሸትን በመደጋገም እውነት ለማድረግ ሲጥሩ አያፍሩም።

የሀገር ቤት እስር ቤቶች ሁሉ እስክንድር ከሌለ የሚዘጉ እስኪመስል ድረስ በተደጋጋሚ የእስርና ሰቆቃ ገፈት ቀማሽ የነበረውን እውነተኛ የመብት ታጋይ እስክንድር ነጋን የወያኔ ሎሌ በማለት ለማሸማቀቅ መሞከር ህሊና ቢስነት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም በጨለማ ደፋፍኖ ለማስቀረት የሚደረግ ሙከራ ብቻ ነው። አክቲቪስትና የምብት ተሚጋች አቻምየለህ ታምሩም ቢሆን ወያኔን በሚጽፋቸው አንጀት አርስ ማስረጃና መረጃ ሙሉ ትችቶቹ ራቁቱን ያስቀረ እውነተኛ ሰው ነው። ይህንን ሰው የግንቦት ሰባት ደጋፊ ባለመሆኑ ብቻ በፍረጃ ከህዝብ ህሊና ለማውጣት የሚደረገው ጥረት የዜግነት ፖለቲካ አራምዳለሁ ለሚል የፖለቲካ ድርጅት ሽንፈት እንጂ ድል ሊሆን አይችልም። በቅርቡ የምርጫ ቦርድ ሃላፊ ሆነው የተሾሙት ወይዘሪት ብርቱካን ስለ ቅንጅት መፍረስ ምክን ያት ተጠይቀው ለመናገር ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ተናግረዋል። ምክ ን ያታቸውን ቢናገሩ

አሁን ወደ ፖልቲካው መዘውር ፊት እየመጡ ያሉትን ዶክተር ብርሃኑን በቀጥታ ስለሚነካ ላለማበላሸት ስለፈለጉ እንጂ የክፍፍሉ መሰረት ዶክተር ብርሃኑ እንደሆኑ በትክክል ያውቁታል። ምክን ያ ቱም ዶክተር ብርሃኑ ትግሬን ከስልጣን አባርሬ የወደቀውን አማራን ለመተካት አልታገልም ብለው በአደባባይ የተናገሩት የኢንጅነር ኃይሉ ተሰሚነትና ሰፊ ድጋፍ ስላቃጠላቸው ነበር።
ልደቱ አያሌው የራሱ የሆነ ችግር የነበረበት ፖለቲካኛ ቢሆንም እንኳ ከቸዋታ ውጪ እንዲሆን የአንበሳውን ድርሻ የተጫዎቱት ዶክተር ብርሃኑ ነበሩ። ይህ ለእውነተኛዋ ኢትዮጵያ በቅንነትና በሃቅ የሚታገሉትን የማሸማቀቅና የማስዎገድ ጉዞ መገታት አለበት። ግንቦት ሰባት ለአዲስ አበባም ሆነ ለቀረው ኢትዮያዊ ቅንጣት ያክል መቆርቆር እንደ ማያሳይ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላላ። ላምሳሌ በቅርቡ በዶክተር አብይ አገዛዝ የኦነግን ባንዲራ የያዛች ሁ ወደ አዲስ አበባ መግባት አትችሉም አሉ በማለት በሃሰት ወጣቶች ታፍሰው ከታሰሩ በኋላ ትምህርት ተሰጧቸው ተለለቀቁ ይባል እንጂ በርካታ ወጣቶች አሁንም በእስር እንዳሉ ያታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በግድያ ወንጀል የተከሰሱ እንዳሉ ያታወቃል። ማንም አእምሮ ያለው መረዳት እንድሚችለው እነኝህ ወጣቶች ምንም አላደረጉም። ነገር ግን ግንቦት ሰባት በዚህ ጉዳይ የወሰደው አንዳችም እርምጃ የለም። በአዲስ አበባ ወረዳዎች ነዋሪ ያልሆኑ በርካታ ሰዎች መታወቂያ እንደተሰጣቸው የሚያሳይ መረጃ ሲዎጣ ግንቦት ሰባት አንዳችም ትንፍሽ አላለም።

ይልቁንም ከኦነጋውያን ጋር በመተባበር እውነትን እያጋለጠ ያለው እስክንድር ነጋ ላይ ዘመቻ እንዲከፈት ተባባሪ ሆኗል።በአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ ላይ በተከፈተው የማጥላላት ዘመቻም ግንቦት ሰባት ተዋናይ ነው። ልዩነቱ በእነ ኢንጅነር ሃይሉ ላይ፣ በእነ ዶክተር ታየ ወልደሰማእት ላይ፣ በእነ ልደቱ አያሌው ላይና በሌሎችም ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኞችና የመብት ተሟጋቾች ላይ እንደተሳካላቸው አሁን እንደማይሳካላቸው አለማዎቃቸው ነው።ግንቦት ሰባት የሃገሪቱን ከ40 በመቶ በላይ የሚወክል የዐአማራ ህዝብ ያልተሳተፈበትን ህገመንግስት በስራ ላይ እንዲቀጥል ይፈልጋል። ግንቦት ሰባት ግንቦት ሰባትን የሚቃወም ፖለቲከኛም ሆነ ጋዜጠኛ እንዲኖር አይፈልግም። ግንቦት ሰባት ለበርካታ አመታት ዐማራን በከፍተኛ አመራሩ አላሳተፈም የሚል ትችት ቢቀርብበትም ጆሮ ዳባ ልበስ ያለ በዚሁም ለመቀጠል የማያቅማማ ስብስብ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄ ከግለሰቦች እውቅና በላይ ነው። በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በተነሱት የማንነት ጥያቄዎች ከሁሉ የሚገርም ጥያቄ ያለው በዐማራው ዘንድ ነው። ዐማራነቴ ይታወቅልኝ ፣ እኔ አማራ ነኝ የሚል ጥያቄ የተነሳው የዐማራ ክልል አስተዳደር ሙስና የሌለበት ወይም መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ስለሆነ

አይደለም። በሰሜን ሸዋ የዐማራ ማንነት ጥያቄ ከባህርዳር ይልቅ አዲስ አበባ ለ አስተዳደር እንደሚቀርብ ይታወቃል። ነገር ግን ህዝቡ እያለ ያለው ዐማራ ነኝ በኦሮሚያ ኦሮሞ ነህ ተብየ መጨፍለቅ የለብኝም ነው። ወልቃይት የአስተዳደርና የልማት ጥያቄ ቢሆን ኖሮ ትግራይ በብዙ መንገድ እንደሚሻለው መገመት አያዳግትም። ነገር ግን ዐማራ መሆኔ ይታወቅልኝ ፤ እኔ ዐማራ እንጂ ትግራይ አይደለሁም ነው ያለው። ራእያ መቀሌ ይቀርበዋል ፣ ነገር ግን ዐማራ ነኝ ብሏል።እነዚህ የማንነት ጥያቄወች ለወያኔ ብቻ ሳይሆን ለግንቦት ሰባትም ምኑም አይደሉም። ዶክተር ብርሃኑ ወልቃይት የማን ነው ተብሎ ሲጠየቅ ኪትዮጵያ ውጪ የሆነ ይመስል ወልቃይት የኢትዮጵያ ነው ሲሉ አሹፈዋል።ምክንያቱም ወልቃይት ዐማራ ነው ቢሉ ከወደ ዐማራ ጠል ቡድኖች የሚመጣባቸውን ትችት አይፈልጉትም።

ዐማራ ለአንዲት ኢትዮጵያ የሞተ አንድነቷንና ክብሯን በጠበቀች ነጻ ሃገር የሚያምን ብርቱ ህዝብ መሆኑን ጠንቅቀው እያዎቁ ዛሬም የዐማራው ብሶት የወለደውን አብን ሲያጥላሉና የጎሳ ፓርቲ ለሀገሪቱ ነቀርሳ ነው ሲሉ ጥቂት እንኳ አይሰቀጥጣቸውም። ዶክተር ብርሃኑ ህብረታቸውም ጋብቻቸውም ከጎሳ ድርጅቶች ጋር ብቻ እንደነበረ ለማንም የተሰወረ አይደለም። ከኦነግ ጋር ከ አንዴም ሁለት ጊዜ ህብረት ፈጥረው ነበር፣ ከ ኦብነግ ጋር፣ ከ አነግ ጋር ከሲነግና ሌሎችም የጎሳ ነጻ አውጪዎች ጋር ተጣምረው ነበር። ዛሬ አብን በፖለቲካ ብስለትና በማስረጃ አሰባሰብ የተሻለ ሆኖ በዐማራው የተፈጸመውን ግፍ በዝርዝር ማሳየት ሲጀመር ግን በዜግነት ፖለቲካ ስም የተሸፈነው ጸረ ዐማራ ማንነት ብቅ አለ። ለዚህ ነው ቴዎድሮስ ጸጋየና እስክንድር ነጋ ሌሎችም ጠንካራ የመብት ተሟጋቾችና ጋዜጠኞች በግንቦት ሰባት መፍያዎች የተለያየ ፍረጃ እየተሰጣቸው ያለው።አዎ ሰለ አገር አንድነት በግንቦት ሰባት ይነገራል፣ እርግጥ ነው ስለ ዜግነት ፖለቲካ ይወራል።

የአንድነት ህብራችን ማሳያ የሆነችዋ አዲስ አበባ በጎሳዎች የባለቤትነት ልፈፋ ውስጥ ስትዎድቅ ግን ስለዚህች ከተማ ግንቦት ሰባት ምንም ማለት አልፈለገም። ሰለ አንድነት የሚሰብከው ግንቦት ሰባት አንድነትን ስለሚያፈራርሰው ህገ መንግስት መለዎጥ ግን አንዳችም ነገር አላለም። ለኢትዮጵያ ህዝብ ቆሚያለሁ መንግስትን እቃወማለሁ የሚለው ግንቦት ሰባት የዐማራ የማንነት ጥያቄም ሆነ መገፋት ምኑም አይደለም።ከዚህ የከፋው ግን ያረጀውና ያፈጀው ብርቅየዎቻችንን ወያኔና የወያኔ ቅጥረኛ በማለት ለማሸማቀቅ የሚያደርገው የማፍያ አካሄድ ነው። ይህን አይነቱ የአንድነት ልፈፋ አገርና አንድነትን የሚያፈርስ እንጂ እውነተኛና ተአማኒ አይደለም። የፍረጃ ካርዳችሁ ተቃጥሏል፤ ከቴዎድሮስ ጸጋየ ፣ ከእስክንድር ነጋ ፣ ከአብን ወይም አቻምየለህ ታምሩን ከመሳሰሉ

በሳል ፖለቲከኞችና የመብት ተሟጋቾች የወመጣን በሳል አስተሳሰብና አመለካከት ወያኔያዊ ነው ብሎ የሚፈርጅ አካል ካለ ግን ራሱ ዎያኔ መሆኑን ያስመሰከረ ብቻ ነው።

የካቲት 2011 ዓም

አዲስ ተስፋ